# የገንዘብ ሚኒስቴር

# MINISTRY OF FINANCE

## መመሪያ ቁጥር 1007/2016

## በቁርጥ በተጣለ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ምጣኔ ላይ ማስተካከያ ለማድረግ የወጣ መመሪያ

## DIRECTIVE NO. 1007/2024
## A DIRECTIVE ISSUED TO MAKE ADJUSTMENTS TO THE SPECIFIC RATES OF EXCISE TAX

ሰኔ 2016 ዓ.ም
June 2024

Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 25 June 2024

## መመሪያ ቁጥር 1007/2016

## በቁርጥ በተጣለ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ምጣኔ ላይ ማስተካከያ ለማድረግ የወጣ መመሪያ

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 10 (2) ከአዋጁ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 1 በተመለከተው የማስከፈያ መጣኔ ላይ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ የዋጋ ንረት ማስተካከያ ሊደረግ እንደሚገባ የሚደነግግ በመሆኑ፤

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ያወጣውን ከ2012 እስከ 2015 በጀት ዓመት ያለውን ዓመታዊ አገራዊ ጠቅላላ ምርት ዲፊሌተር መረጃ በመጠቀም በአልኮል መጠጦች፤ በትምባሆና በትምባሆ ውጤቶች እንዲሁም በፕላስቲክ ከረጢት ላይ በቁርጥ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ ማስተካከል በማስፈለጉ፤

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 10 (2 ) እና 42 (2) ለገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በቁርጥ በተጣለ የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ ላይ ማስተካከያ ለማድረግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 1007/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ማስተካከያ ስለማድረግ

ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 (እንደተሻሻለ) ጋር በተያያዘው የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ሰንጠረዥ ውስጥ የማስከፈያ ምጣኔያቸው

## DIRECTIVE NO. 1007/2024

## A DIRECTIVE ISSUED TO MAKE ADJUSTMENTS TO THE SPECIFIC RATES OF EXCISE TAX

Whereas, Article 10 (2) of the Excise Tax Proclamation No. 1186/2020 (as amended) provides that inflation adjustment shall be made at least once a year on the specific rates of excise tax provided under Table 1 attached to the Proclamation in accordance with the directives issued by the Ministry of Finance;

Whereas, it has become necessary to make adjustment on the specific excise tax rates imposed on the alcoholic beverages; tobacco and tobacco products as well as plastic bags using the annual national gross product deflator data from 2020 to 2023 fiscal year issued by the Ministry of Planning and Development,;

Now therefore, in accordance with Article 10 (2) and 42(2) of Excise Tax Proclamation No. 1186/2020 (as amended), the following Directive has been issued by the Ministry of Finance.

### 1. SHORT TITLE

This directive may be cited as "Directive No. 1007/2024 to make adjustments to the specific rates of excise tax ".

### 2. ADJUSTMENTS

The specific excise tax rates determined by the Excise Tax Proclamation No. 1186/2020 (as amended) that are applicable to alcoholic beverages, Tobacco and Tobacco Products and Plastic Bags are

በቁርጥ የተወሰነው የአልኮል መጠጦች፤ ትምባሆ እና የትምባሆ ውጤቶች እንዲሁም የፕላስቲክ ከረጢት የማስከፈያ መጣኔ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው የማስከፈያ መጣኔ ተተክቷል።

hereby replaced by the Schedule of tax rate attached to this directive.

## 3. የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ድህረ-ገፀ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ 2016 ዓ.ም
አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር

## 3. EFFECTIVE DATE

This Directive shall enter into force as of the date of its registration on the Ministry of justice and its uploading on the official website of the Ministry of Finance.

Addis Ababa may 2024

Ahmed Shide

Minister of Finance

Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 25 June 2024

**አባሪ**
**Annex**

## ሀ. የአልኮል መጠጦች እና የፕላስቲክ ከረጢት(ፌስታል) ኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ
A. Excise tax rate on alcoholic beverages and plastic bags

| ታሪፍ ቁጥር<br>Tariff No. | የዕቃ ዓይነት<br>Description | የተስተካከለው ኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|
| 2203.0000 | ከብቅል የተዘጋጀ ቢራ<br><br>Beer made from malt | 40% ወይም 28ብር በሊትር ከሁለቱ አንዱ የበለጠውን<br><br>40% or 28 birr per litter whichever is higher |
| | ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ ተመርቶ በበቀለ ገብስ የተመረተ ቢራ<br><br>Beer produced exclusively from barley grown and malted in Ethiopia | 35% ወይም 23 ብር በሊትር ከሁለቱ አንዱ የበለጠውን<br><br>35% or 23 birr per litter whichever is higher |
| | ውሃን ሳይጨምር ቢያንስ ከክብደቱ 75% የሚያህለው በአገር ውስጥ ግብዓት የተመረተ ቢራ<br><br>Beer the local raw material content of which excluding water is at least 75% by weight of its constituents | 30% ወይም 21 ብር በሊትር ከሁለቱ አንዱ የበለጠውን<br><br>30% or 21 birr per litter whichever is higher |
| 2206.0000 | የሚፈሉ መጠጦች (ሲዳር፣ ፔሪ፣ ኦፓክ ቢራ፣ የሩዝ አልኮል መጠጥ)፣ የሚፈሉ መጠጦችና የአልኮል አልባ መጠጦች ድብልቅ፣ ስታውት፣ ሌሎች ከቢራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መጠጦች፣ ዱቄት ቢራ፣ የአልኮል ይዘታቸው ከ7% ያልበለጠ<br><br>Fermented Beverages(for example, Cider, Perry, mead, sake, Opaque beer) and with mixtures of fermented beverages with non-alcoholic beverages and of other beer kind, powdered beer, of an alcoholic content not more than 7% by volume | 40% ወይም 28 ብር በሊትር ከሁለቱ አንዱ የበለጠውን<br><br>40% or 28 birr per litter whichever is higher |

| | | |
|---|---|---|
| 2208.9010 | በድብልቅ የተዘጋጁ፣ የአልኮል ይዞታቸው ከ7% ያልበለጠ ጥንካሬ ያላቸው መጠጦች<br><br>Ready to drink mixtures of an alcoholic content not exceeding 7% vol | 40% ወይም 28 ብር በሊትር ከሁለቱ አንዱ የበለጠውን<br><br>40% or 28 birr per litter whichever is higher |
| 3923.2110<br>3923.2910 | የፕላስቲክ ከረጢት(ፌስታል)<br>Shopping plastic bags | 103 ብር በኪሎግራም<br>103 birr per Kg |

## ለ. ትምባሆና የትምባሆ ውጤቶች የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ

B. Excise tax on tobacco and tobacco products

| ታሪፍ ቁጥር<br>Tariff No. | የዕቃ ዓይነት<br>Description | የተስተካከለው የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|
| 2402.1000 | ትምባሆ የያዙ ሲጋሮች፣ ቼሩትስና ሲጋሪሎስ<br>Cigars, cheroots and cigarillos, containing tobacco | 30% + 644 ብር በኪሎግራም<br>30% +(plus) 644 birr per kilogram |
| 2402.2000 | ትምባሆ የያዙ ሲጋራዎች<br><br>Cigarettes containing tobacco | 30%+20ብር በፓኬት ( 20 ፍሬ)<br><br>30% +(plus) 20 birr per pack(20 sticks) |
| 2402.9000 | እንደ ትምባሆ ከሚያገለግሉ የተዘጋጁ ሲጋሮች፣ ቼሩትስና ሲጋሪሎስ እና ሲጋራዎች<br>Cigars, cheroots and cigarillos, cigarettes of tobacco substitutes | 30%+20ብር በፓኬት ( 20 ፍሬ)<br><br>30% +(plus) 20 birr per pack(20 sticks) |
| 2403.1900 | የሚጨስ ትምባሆ፣ በማናቸውም ምጣኔ እንደ ትምባሆ የሚያገለግሉ ነገሮችን የያዘ ቢሆንም (የፍራፍሬ ጣዕም እንዲኖራቸው የተደረጉም ያልተደረጉም የትምባሆና ግላይሰሮል ቅልቅል የያዘ ትምባሆ ለማጨስ የሚያገለግል በውሃ ማስተላለፊያ ቱቦ የሚጨስ መዓዛ ሰጭ ዘይት እና ምዝሞዞች፣ ሞላሰስ ወይም ስኳር ከተጨመረባቸውም ሆነ ካልተጨመረባቸው በስተቀር) | 30%+644 በኪሎግራም<br><br>30% +(plus) 644 birr per kilogram |

| | | |
|---|---|---|
| | Smoking tobacco, whether or not containing tobacco substitutes in any proportion other than tobacco intended for smoking in a water pipe and which consists of a mixture of tobacco and glycerol, whether or not containing aromatic oils and extracts, rnolasses or sugar, and whether or not flavoured with fruit. | |
| 2403.9100 | “የተዋሐደ” ወይም “እንደገና የተዘጋጀ” ትምባሆ<br>“Homogenised” or “reconstituted” tobacco | 30%+644ብር በኪሎግራም<br><br>30% +(plus) 644 birr per kilogram |
| 2403.9900 | ሱረት፣ የትምባሆ ምዝምዞችና ኤሰንሶች<br>Snuff, tobacco extracts and essences | 30%+644ብር በኪሎግራም<br><br>30% +(plus) 644 birr per kilogram |